DISTRICT OF COLUMBIA
PUBLIC SCHOOLS

# የDCPS የተማሪ መመሪያ፤ ወደ ምረቃ፣ የስራ-መስክ፣ እና ኮሌጅ - ተደጋግመው የሚጠየቁ ጥያቄዎች

*ይህ የመረጃ ምንጭ (resource)፣ ከሌሎች መመሪያዎች ጋር በ: https://dcpsgoestocollege.org/guide-resources/ መገኘት ይችላል።

## አጠቃላይ ተደጋግመው የሚጠየቁ ጥያቄዎች (GENERAL FAQS)

**መረጃው የሚያንጸባርቀው የትኛውን ቀን ነው?**
**ሴፕቴምበር (September) 3 ቀን 2021** ከዚህ ቀን በኋላ፣ የግምገማ ሥልት ውጤቶች መረጃዎችን ጨምሮ፤ በዚህ መመሪያ ውስጥ አይንጸባረቁም።

**በመመሪያ ውስጥ የተማሪው መረጃ የተገኘው ከየት ነው?**
መረጃ ዝርዝሩ (data) የወጣው፣ ከ'Aspen'፣ 'Naviance'፣ እና ከድህረ-ሁለተኛ ደረጃ የዳሰሳ ጥናቶች ነው።

**የመመሪያውን የዲጂታል ስሪት (digital version)፣ ከየት ነው የማገኘው?**
የዲጂታል ስሪቶቹ (digital versions) በአስፐን (Aspen) ላይ ይገኛል። ወላጆች እና ቤተሰቦች፤ የአስፐን የወላጅ ፖርታል (Aspen Parent Portal)ን በwww.bit.ly/ParentPortalDCPS ላይ መጎብኘት ይችላሉ።

**በየስንት ጊዜው ነው መመሪያውን የማገኘው?**
መመሪያው ለሲኒየሮች (seniors)፣ በበልግ (fall) ወቅት እና ከ9 -11 ክፍል ተማሪዎች ደግሞ በፀደይ (spring) ሴሚስተር ወቅት፣ የሚገኝ ይሆናል።

**መመሪያው በምን ቋንቋዎች ነው የሚገኘው?**
መመሪያው፤ በአማርኛ፣ በቻይኒኛ፣ በእንግሊዘኛ፣ በፈረንሳይኛ፣ በስፓኒሽ እና ቬትናም ቋንቋዎች ይገኛል። እያንዳንዱ ወላጅ፣ የእንግሊዘኛ ቅጂውንም ያገኛሉ።

**በመመሪያዬ ላይ የተዛባ መረጃ ቢኖር፣ ማድረግ ያለብኝ ምንድን ነው?**
እባክዎን፣ በDCPSguide@k12.dc.gov ኢሜል ያድርጉ እና ካውንስለርዎን ያነጋግሩ። የትምህርት ቤት አማካሪዎ (ካውንስለርዎ)፣ ወቅታዊ የሆነ መረጃዎ ይኖረዋል።

**መመሪያዬን፣ እነማን ማግኘት ይችላሉ?** ካውንስለሮች፣ የኮሌጅ እና የስራ-መስክ አስተባባሪዎች፣ አስተማሪዎች፣ እና የትምህርት ቤት አስተዳደሮች። በተጨማሪም፣ ትምህርት ቤትን መሠረት ያደረጉ አጋር-የትብብር ድርጅቶች፤ የDCPS ተማሪዎችን የሚያገለግሉና የመረጃ ስብስቦችን የደህንነት ጥበቃ ዋስትና ቃል-

## የትምህርት ውጤት ማስረጃ እና የምረቃ ገጽ፣ ተደጋግመው የሚጠየቁ ጥያቄዎች (TRANSCRIPT AND GRADUATION PAGE FAQS)

ኪዳን የፈረሙ፤ ለተወሰኑ ብቻ የሚያገለግሏቸው ተማሪዎች መረጃዎችን ማግኘት ይችላሉ።

**በመመሪያው ውስጥ የሚገኘው የትምህርት ውጤት ማስረጃ (transcript)፣ ህጋዊ (official) የትምህርት ውጤት ማስረጃ (transcript) ነው?** የለም፣ አይደለም። ህጋዊ (official) የትምህርት ውጤት ማስረጃ (transcript)፣ በትምህርት ቤት ኃላፊ (አስተዳዳሪ ወይም ካውንስለር) ህጋዊ ፊርማ የተፈረመበት መሆን አለበት። አብዛኞዎቹ ተቀባይ የሆኑ ተቋማት፣ የትምህርት ውጤት ማስረጃው ህጋዊነት (official) ሆኖ እንዲቆጠር የታሸገ እንዲሆን ይጠይቃሉ።

**በመመሪያው ውስጥ የትምህርት ውጤት ማስረጃ (transcript) ከሌለስ?**

በመመሪያቸው ውስጥ የትምህርት ውጤት ማስረጃ (transcript) የሌላቸው ተማሪዎች፤ **ሴፕቴምበር (September) 3 ቀን 2021፣** መረጃ በተወሰደበት ጊዜ፣ በፋይል ውስጥ የትምህርት ውጤት ሪከርድ ያነበራቸው ናቸው። እነዚህ ተማሪዎች ከትምህርት ቤት ካንውንስለራቸው ጋር መገናኘት አለባቸው።

**በተመራቂዎች ገጽ ላይ በትክክለኛው የስኬት ጉዞ ላይ/ከስኬት ጉዞ ውጪ ደረጃዬ የሚወሰነው እንዴት ነው?**

ይህ ደረጃ የሚወሰነው፣ ተማሪው በሰዓቱ ለመመረቅ የሚጠበቀውን ማለፊያ ነጥብ አሟልቶ የሚገኝ መሆን አለመሆኑ፤ በአሁኑ ሰዓት ቁልፍ በሆኑ የትምህርት ዓይነቶች ተመዝግቦ እንደሆነ ነው። ተማሪው አስፈላጊ በሆነ መሟላት በሚገባው ትምህርት ያላለፈ ከሆነ ወይም ማሟላት በሚጠይቅ የትምህርት ዓይነት፤ የተማረ ሆኖ ካልተገኘ "ከመስመር ውጪ" ሊሆን ይችላል።

**እያንዳንዱ ምልክት የሚደረግበት-ቦታ የሚወክለው፣ ምን ያህል የኮርስ ክሬዲቶችን ነው?**

እያንዳንዱ ምልክት ማድረጊያው (check mark)፣ .5 ክሬዲቶችን ይወክላል።

**የክፍል ደረጃዬ የሚወሰነው እንዴት ነው?**

የክፍል ደረጃ ቀጥታ የሚወሰደው ከአስፐን (Aspen) ሲሆን፣ **ከሴፕቴምበር (September) 3 ቀን 2021** ጀምሮ ያለውን የክፍል ደረጃ ያንፀባርቃል። የተገኙትን ክሬዲቶች ቁጥርን እና፤ እንደ እንግሊዘኛ ወይም ሂሳብ ባሉ ቁልፍ ትምህርቶች ማለፍንም ያንፀባርቃል።

**የትምህርት ውጤት ማስረጃዬ (transcript) ወይም የደረጃ ውጤቴ የተዛባ ከሆነስ ምን ይሆናል?**

በመጀመሪያ፤ ከትምህርት ቤት አማካሪያችሁ ጋር መነጋገር ይኖርባችኋል። እባክዎን፤ በDCPSguide@k12.dc.gov ኢሜልም ይላኩ።

**የበልግ (fall) ሴሚስተር የውጤት ደረጃዎች፣ በትምህርት ውጤት ማስረጃው (transcript) ላይ የሚታይ ይሆናል?**

ለማንኛውም የጊዜ-ሰሌዳ ለተሰጣቸው ኮርሶች፣ የትምህርት ዓይነት ስም እና የኮርሱ ኮድ ቁጥር በትምህርት ውጤት ማስረጃው ላይ የሚሰፍሩ ሲሆን፣ ኮርሱ ተጠናቆ እስካላበቃ ድረስ የውጤት ደረጃዎቹ አይታዩም፤ ይህም 0.5 (የግማሽ ዓመት ኮርሶችን) ያካትታል።

## **የኮሌጅ ገጽ፣ ተደጋግመው የሚጠየቁ ጥያቄዎች (COLLEGE PAGE FAQS)**

**በእያንዳንዱ በተዘጋጁት ኮሌጅ ውስጥ ምን ያህል የመግቢያ (admission) ዕድሎች ይኖራሉ እና ይህም ሊቀየር ይችላል?**

የመግባት ዕድሉ መሠረት ያደረገው፣ በተማሪው የGPA እና የ(P)SAT የውጤት ደረጃው (score)፣ ከዚህ ቀደም በናቪያንስ (Naviance) ላይ ከነበረ የDCPS የማመልከቻ የመረጃ ስብስብ (data) ጋር ተነፃፅሮ ይሆናል። ያስታውሱ: ብዙ ምክንያቶች በመግቢያ (admission) ውስጥ የሚካተቱ እና የመግቢያ (admission) ተወዳዳሪነትን ለማሳደግ ምንግዜም ቢሆን ጊዜ ይኖራል!

**አዲሱን የኮሌጅ መዘጋጃ-ገጽ (prep page) እንዴት ነው መጠቀም የምችለው?**

አዲሱ የኮሌጅ መዘጋጃ-ገጽ (college prep page)፤ ስለ ኮሌጅ መግቢያ ሂደቶች ዋናዎቹን ክፍሎች እናንተን እና ቤተሰባችሁ በተሻለ ሁኔታ እንድትረዱት ለማገዝ የተዘጋጀ ነው። በ4-ዓመቱ የከፍተኛ ደረጃ ትምህርታችሁ ጊዜ የነበራችሁ GPA፣ የፈተና ውጤቶች፣ ከትምህርት-ውጪ የነበሩ እንቅስቃሴዎች (extracurriculars) እና የሚሰጠው የኮርስ መጠኖች፤ ወደ ተለያዩ ኮሌጆች ተቀባይነትን ሊያስገኙችሁ የመቻል አዝማሚያው ላይ ያለው ተጽዕኖ እንዴት እንደሆነ መገንዘብ፤ የኮሌጅ ዕቅድን ወደ መቅረጽ የሚደረግ የመጀመሪያ እርምጃ ነው።

**የእኔ PSAT/SAT ውጤት የት ነው?**

በCOVID-19 ምክንያት፤ DCPS፣ PSAT እና SATን ለተማሪዎቹ መስጠት አልቻለም ነበር። የጤና ሁኔታዎች ሲፈቅዱ፣ በኦክቶበር (October) 2021 ፈተናውን ለመስጠት፣ DCPS ያቅዳል።

**ኮሌጆቹ ተመርጠው የነበሩት እንዴት ነበር?**

ይህ ከእያንዳንዱ የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ማመልከቻቸው ካስገቡት ተማሪዎች፣ በተማሪ ስኬት ጠንካራ-ቁጥርን በማስመዝገብ በታሪካዊ ታዋቂነት ላይ መሠረት ባደረገ ሁኔታ፣ ለናሙና የቀረበ የኮሌጆች ዝርዝር ነው። ኮሌጆችን እንዴት መፈለግ እንደሚቻል የበለጠ ለማወቅ፣ የናቪያንስ (Naviance) ቪዲዮአችንን በ [http://bit.ly/naviancesupermatch](http://bit.ly/naviancesupermatch) ተመልከቱ።

** ማስታወሻ፣ የኮሌጅ ዝርዝሩ፣ ለማንኛውም ይሄ-ነው ለተባለ ተማሪ፤ ሁሉንም አጠቃላይ የአማራጭ ስፋቱን አንጸባርቆ ያሳየ አይደለም።*

**የናቪያንስ (Naviance) ገጼን ማግኘት የምችለው የት ነው፤ እና እንዴት ነው መግባት (login ማድረግ) የምችለው?**

ወደ: [www.clever.com](http://www.clever.com) ሂዱ።

የተጠቃሚ ስም (username): studentIDnumber@students.k12.dc.us
የሚስጥር ቁልፎች (Passwords): (የተማሪው የልደት ቀን ነው): ወርቀንዓ.ም (mmddyy)

* የNaviance ገጽን ወደእናንተ ለማምጣት፣ በNaviance ምልክት (Icon) ላይ መጫን

## **የስራ-መስክ ገጽ፣ ተደጋግመው የሚጠየቁ ጥያቄዎች (CAREER PAGE FAQS)**

**የስራ-መስክ ስብስቦች (clusters)፣ እንዴት ነው የተመረጡት?**

የስራ-መስክ ስብስቦች (clusters) የተማሪዎች ምላሾችን፣ ለድኅረ-ሁለተኛ ደረጃ የዳሰሳ ጥናት መሠረት ያደረገ ነበር። ተማሪው የዳሰሳ ጥናቱን ካላጠናቀቀ፣ የ3 የዲሲ አካባቢ ከፍተኛ የዐበል/ከፍተኛ ፍላጎት ባላቸው የስራ-መስክ ስብስቦች (clusters)ን እንዲውጣጡ አድርጎታል። የ'Business Administration'፣ የ'Information Technology (IT)'፣ እና የ'Health Sciences' ናቸው።

**በስራ-መስክ ገጽ ላይ ጎልተው የተቀመጡት ኮሌጆች እና ስለ ተጨማሪ የስራ-መስኮች እና ኮሌጆች መማር የምችለው የት ነው?**

ስለኮሌጆች እና የስራ-መስኮች፣ የበለጠ በስፋት ለማወቅ፤ ናቪያንስ (Naviance) አንዱ ግሩም የሆነ ቦታ ነው::

## **የሚወሰዱ እርምጃዎች ገጽ፣ ተደጋግመው የሚጠየቁ ጥያቄዎች (ACTION STEP PAGE FAQS)**

**የተማሪው ድኅረ-ሁለተኛ ደረጃ ጥርጊያ ጎዳናው ግብ (post-secondary pathway) የሚወሰነው እንዴት ነበር?**

የድኅረ-ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የመሸጋገሪያ ጥርጊያ ጉዳና ግብ ተወሰኖ የነበረው፣ ለሁለተኛ ደረጃ የዳሰሳ ጥናት ተማሪዎች በሰጡት ምላሾች መሠረት ነው። *ማስታወሻ:* የድኅረ-ሁለተኛ ደረጃ የዳሰሳ ጥናትን ያላጠናቀቁ ተማሪዎች፣ ተዘርዝሮ የተቀመጠ የሽግግር ግቦች (pathway goal) አይኖራቸውም።

**ለምንድን ነው ሁሉንም የሽግግር መንገዶች እና (pathways and steps) እርምጃዎችን እንድመለከት የተደረገው?**

እያንዳንዱ ተማሪ ከምረቃ በኋላ፣ ወደሚቀጥለው እርምጃዎቹ እንዲዘጋጅ እንፈልጋለን። በሚወሰድ እርምጃ ገጽ (action step page) ላይ፣ እያንዳንዱ ተማሪ መቀጠል በሚፈልግባቸው በማናቸውም የሽግግር ጥርጊያ መንገድ (pathway) ላይ ቁልፍ የሆኑ የሚወሰዱ እርምጃዎችን ያገኛሉ። እርምጃዎቹ ለሲኒየሮች (seniors) እንዲስማሙ ሆነው የተዘጋጁ ናቸው።

## **ስለ ቀጣይ እርምጃዎች ተደጋግመው የሚጠየቁ ጥያቄዎች (NEXT STEPS FAQS)**

**መመሪያው ከደረሰኝ በኋላ፣ የተማሪውን የእድገት-ሂደት እንዴት መቆጣጠር እችላለሁ?**

ለተማሪዎች: ወደ አስፒን (Aspen) እና ናቪያንስ (Naviance) ፖርታል በመሄድ፤ ወቅቱን የተጠበቀ መረጃ ማግኘት ይችላል። ካውንስለራችሁንም ማነጋገር ሊኖርባችሁ ይችላል።

ወላጆች: የአስፐን የወላጅ ፖርታል (Aspen Parent Portal)ን በ [www.bit.ly/ParentPortalDCPS](http://www.bit.ly/ParentPortalDCPS) ላይ መጎብኘትም ትችላላችሁ።

**ፕሮግራሞች፣ ለእኔ ሊቀርቡ የሚችሉት እነዚሁ ብቻ ናቸው?**

የለም፣ አይደለም። በስራ-መስክ ገጽ ላይ ጎልተው የተቀመጡት ኮሌጆች፤ በስራ-መስኩ ስብስቦች (clusters) ጋር ግንኙነት የነበራቸው ፕሮግራሞች አቅርቧል። እነዚህ የቀረቡት፣ ለናሙናነት ብቻ እና ሁሉንም አጠቃላይ የአማራጭ ስፋቱን አያንጸባርቁም።

**የዐበል እና የደሞዝ መረጃዎች፣ እንዴት ነው የተወሰኑት?** ለዲሲ የሜትሮ አካባቢ፣ የዐበል እና የደሞዝ መረጃዎች የተወሰዱት፣ ከ'Bureau of Labor and Statistics (BLS)' ነው።

**ለመመሪያው ተጨማሪ የመረጃ ምንጮችን (resources) ከየት ማግኘት እችላለሁ?** ለተጨማሪ የመረጃ ምንጮች (resources)፣ እባክዎን: https://dcpsgoestocollege.org/guide-resources/ ይጎብኙ።

**ስለ መመሪያው ወይም ስለ ድኅረ-ሁለተኛ ደረጃ የሽግግር ጎዳና፤ ተጨማሪ ጥያቄዎች ካሉኝ ማንን ነው ማነጋገር**

**ያለብኝ?**
በመጀመሪያ በመመሪያው መግቢያ ገጽ ላይ የሰፈሩት ካውንስለር ወይም የኮሌጅና የስራ-መስክ አስተባባሪውን ማነጋገር ይኖርብዎታል።

ስለመመሪያው አጠቃላይ ጥያቄዎች ካሉ፣ ወደ DCPSguide@k12.dc.gov ሊላኩ ይችላሉ።

DISTRICT OF COLUMBIA
PUBLIC SCHOOLS

# የDCPS የተማሪ መመሪያ፤ ወደ ምረቃ፣ የስራ-መስክ፣ እና ኮሌጅ - ተደጋግመው የሚጠየቁ ጥያቄዎች፤ ለምስክር-ወረቀት መከታተያ ስሪት (Version)

*ይህ የመረጃ ምንጭ (resource)፣ ከሌሎች መመሪያዎች ጋር በ: https://dcpsgoestocollege.org/guide-resources/ መገኘት ይችላል።

## አጠቃላይ ተደጋግመው የሚጠየቁ ጥያቄዎች (FAQS)

**መረጃው የሚያንጸባርቀው የትኛውን ቀን ነው?**
**ሴፕቴምበር (September) 3 ቀን 2021** ከዚህ ቀን በኋላ፣ የግምገማ ሥልት ውጤቶች መረጃዎችን ጨምሮ፤ በዚህ መመሪያ ውስጥ አይንጸባረቁም።

**በመመሪያ ውስጥ የተማሪው መረጃ የተገኘው ከየት ነው?**
የመረጃ ዝርዝሩ (data)፣ ከአስፐን (Aspen)፣ ናቪያንስ (Naviance) እና ከልዩ ትምህርት የመረጃ ስብስብ ዘዴ (Special Education Data System (SEDS)፤ የተውጣጡ ናቸው።

**የመመሪያውን የዲጂታል ስሪት (digital version)፣ ከየት ነው የማገኘው?**
የዲጂታል ስሪቶቹ (digital versions) በአስፐን (Aspen) ላይ ይገኛል። ወላጆች እና ቤተሰቦች የአስፐን የወላጅ ፖርታልን (Aspen Parent Portal) በwww.bit.ly/ParentPortalDCPS ላይ መጎብኘት ይችላሉ።

**በየስንት ጊዜው ነው መመሪያውን የማገኘው?**
መመሪያው ለC4 pathway ተማሪዎች)፣ በበልግ (fall) ወቅት እና ከC1-C3 pathways ተማሪዎች ደግሞ በፀደይ (spring) ሴሚስተር ወቅት፣ የሚገኝ ይሆናል።

**መመሪያው በምን ቋንቋዎች ነው የሚገኘው?**
መመሪያው፤ በአማርኛ፣ በቻይኒኛ፣ በእንግሊዘኛ፣ በፈረንሳይኛ፣ በስፓኒሽ እና ቬትናም ቋንቋዎች ይገኛል። እያንዳንዱ ወላጅ፣ የእንግሊዘኛ ቅጂውንም ያገኛሉ።

**በመመሪያዬ ላይ የተዛባ መረጃ ቢኖር፣ ማድረግ ያለብኝ ምንድን ነው?**
እባክዎን፣ በDCPSguide@k12.dc.gov ኢሜል ያድርጉ እና ካውንስለርዎን ያነጋግሩ። የትምህርት ቤት አማካሪዎ (ካውንስለርዎ)፣ ወቅታዊ የሆነ መረጃዎ ይኖረዋል።

**መመሪያዬን፣ እነማን ማግኘት ይችላሉ?** ካውንስለሮች፣ የኮሌጅ እና የስራ-መስክ አስተባባሪዎች፣ አስተማሪዎች፣ የግል የትምህርት ፕሮግራም (Individualized Education Program (IEP) ጉዳይ አስፈጻሚዎች፣ እና የትምህርት ቤት አስተዳደሮች። በተጨማሪም፣ ትምህርት ቤትን መሠረት ያደረጉ አጋር-የትብብር ድርጅቶች፤ የDCPS ተማሪዎችን የሚያገለግሉና የመረጃ ስብስቦችን የደህንነት ጥበቃ ዋስትና ቃል-ኪዳን የፈረሙ፤ ለተወሰኑ ብቻ የሚያገለግሏቸው ተማሪዎች መረጃዎችን ማግኘት ይችላሉ።

**የክፍል ደረጃዬ የሚወሰነው እንዴት ነው?**
የክፍል ደረጃ ቀጥታ የሚወሰደው ከአስፐን (Aspen) ሲሆን፣ **ከሴፕቴምበር (September) 3 ቀን 2021** ጀምሮ ያለውን የክፍል ደረጃ ያንፀባርቃል። በተማሪው የግል የትምህርት ፕሮግራም (Individualized Education Program (IEP) ላይ በተቀመጠው መሠረትም፣ የተማሪውን የምረቃ የሽግግር ጎዳና (pathway) ያንፀባርቃል።

## <u>ድኅረ-ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት፤ ተደጋግመው የሚጠየቁ ጥያቄዎች (POSTSECONDARY EDUCATION FAQS)</u>

**የድኅረ-ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ፕሮግራሞች ተመርጠው የነበሩት እንዴት ነው?**
የተዘረዘሩት ፕሮግራሞች በሙሉ በአካባቢው ውስጥ የሚገኝ ሲሆኑ እና የመማር እና የእድገት እክሎች (intellectual and developmental disabilities) ላለባቸው ተማሪዎች የሚሰጡ ናቸው። የፕሮጀክት ሰርች (Project SEARCH) እና የሪቨር ቴራስ (River Terrace): የሥራ-ኃይል እድገት ማዕከል (Workforce Development Center)፤ ስለ እንግዳ-አቀባበል (hospitality)፣ ስለ ጤና ሣይንስ (health sciences)፣ እና ስለ ጓሮ አትክልት አያይዝ (horticulture)፤ ልዩ የሆኑ የሙያ-ሥልጠናን ብቻ፣ ለDCPS አመልካቾች የሚሰጡ ናቸው።

**የNaviance ገጼን ማግኘት የምችለው የት ነው፤ እና እንዴት ነው መግባት (login ማድረግ) የምችለው?**

ወደ: www.clever.com ሂዱ።

የተጠቃሚ ስም (username): studentIDnumber@students.k12.dc.us

የሚስጥር ቁልፎች (Passwords): (የተማሪው የልደት ቀን ነው): ወርቀንዓ.ም (mmddyy)

* የNaviance ገጽን ወደእናንተ ለማምጣት፣ በNaviance ምልክት (Icon) ላይ መጫን

**ወደ የሥራ-ኃይል (workforce) እና/ወይም ወደ ድኅረ-ሁለተኛ ደረጃ ሥልጠና ለመግባት፤ ስለተጨማሪ ድጋፎች ከየት ማወቅ እችላለሁ?**

መልሶ የማቋቋም አገልግሎቶች አስተዳደር (Rehabilitation Services Administration (RSA)፣ እክል ላለባቸው ጎልማሶች የሙያ ዝግጁነት ድጋፍ የሚሰጥ ድርጅት ነው። ተማሪዎች ከRSA አገልግሎቶች ጋር በመመዝገብ (signing up) በማድረግ አገልግሎቶችን ለማግኘት፤ ከግል የትምህርት እቅድ (IEP) ጉዳይ አስፈፃሚ ጋር ግንኙነት ማድረግ አለባቸው።

## <u>ስለ ቀጣይ እርምጃዎች ተደጋግመው የሚጠየቁ ጥያቄዎች (NEXT STEPS FAQS)</u>

**ሰለ መመሪያው ወይም ስለ ድኅረ-ሁለተኛ ደረጃ የሽግግር ጎዳና፤ ተጨማሪ ጥያቄዎች ካሉኝ ማንን ነው ማነጋገር ያለብኝ?**
በመጀመሪያ በመመሪያው መግቢያ ገጽ ላይ የሰፈሩት ካውንስለር፣ የIEP ጉዳይ አስፈፃሚ ወይም የኮሌጅና የስራ-መስክ አስተባባሪውን ማነጋገር ይኖርብዎታል። ስለመመሪያው አጠቃላይ ጥያቄዎች ካሉ፣ ወደ DCPSguide@k12.dc.gov ሊላኩ ይችላሉ።